# Union of Tigreans in North America (UTNA)
## ማሕበር ተጋሩ ሰሜን ኣሜሪካ (ማተሰኣ)

UTNA
P.O.BOX 73736
Washington, DC 20056
UTNA67@verizon.net

Tel. (202) 265-8702
Fax. (202) 265-8703


November 2/2009

### የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ስነ-ምግባር ደንብ ላይ ያደረጉት ስምምነትን አስመልክቶ ከትግራይ ተወላጆች ማህበር በሰሜን አሜሪካ የተሰጠ መግለጫ

ሃገራችን ኢትዮጵያ ለዘመናት በላይዋ ላይ ተጭነውባት የነበሩት የአድልዎና ኋላቀር ስርዓታት ለማስወገድ ባደረገችው መራራ ትግል በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ልጆቿ መስዋእትነት የከፈሉበት፣ የጀግኖች ልጆቿ ደም በየዱር ገደሉና ሸንተረሩ ያፈሰሱበት ውጤት እነሆ ዛሬ

- የሁሉም ብሄር ብሄረሰብ ህዝቦች በራሳቸው ባህል፣ቋንቋና ታሪክ ኮርተው ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩበት ሙሉ መብት ኖሯቸው በእኩልነትና መከባበር የተመሰረተ ኣንድነት እውን እየሆነ ባለበት፣
- የኢትዮጵያ ዋና ጠላት የሆነውን ድህነት ከስረ መሰረቱ ለማስወገድ እልህ አስጨራሽ ርብርብ እየተደረገ ባለበት፣ በኢንቨስትመንት መስህብነቷ ታላቅ ትኩረት ባገኘችበትና ሁለገብ የመሰረተ ልማት ግንባታ በሃገራችን ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ እተፋጠነ ባለበት፣
- የአፍሪካ አንገብጋቢ ጉዳዮችን በዓለም አቀፋዊ መድረኮች ቀርበው እንዲታዩና መፍትሄ እንዲያገኙ በማድረግ ዘንድ ታላቅ ሚና በመጫወቷ ምክንያት ልዩ ክብር በተጎናፀፈችበት ወቅት ጎን ለጎን መጪው ግንቦት ላይ የሚካሄደው 4ኛው ሃገራዊ ምርጫ ግልፅ፣ ነፃ፣ ፍትሃዊና ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን በገዢው ፓርቲ ኢ.ህ.ኣ.ዴ.ግና ተቃዋሚ ፓርቲዎች ማለትም በኢንጅነር ሃይሉ ሻውል የሚመራው የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መ.ኢ.ኣ.ድ)፣ በአቶ ልደቱ ኣያሌው የሚመራው የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኢ.ዴ.ፓ)ና በአቶ አየለ ጫሚሶ የሚመራው ቅንጅት ለአንድነትና ዴሞክራሲ ፓርቲ ላለፉት ሁለት ወራት በምርጫ ስነ-ምግባር ደንብና በደንቡ ማስፈፀሚያ መመሪያ ሰፊ ውይይት በማካሄድ ሁለቱም ወገኖች ህገ-መንግስቱ ያጎናፀፈውን መብትና ግዴታ ሳይሸራረፍ ለመተግበር በሚያስማሙዋቸው ላይ አብሮ በመስራት የሚያለያዩዋቸው ነጥቦች በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንገድ በጠረጴዛ ዙሪያ በመወያየት ልዩነቶችን በማጥበብና በመቻቻል በክቡር መስዋእትነት የተገኘውን የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ጅማሮ ለማጠናከር ወስነው መስማማታቸው የተሰማንን ታላቅ ደስታ ስንገልፅ ይህንን መልካም ዓላማ እውን ለማድረግ የገዢው ፓርቲ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መላውን የኢትዮጵያ ህዝብ በማስተባበር ፈፅሞ የማይነካ

ይመስል የነበረውን የደርግ ስርዓት ከገረሰሰ በኋላ ጊዜ ሊወስድ የግድ ቢሆንም የዴሞክራሲና ሰብአዊ መብት ሽታ ካልነበረበት ከባዶ ተነስቶ ትእግስትና ጥበብን ተላብሶ ለሃገራችን ብልፅግናና መሻሻል ሲባል አብሮና ተቻችሎ በሰጥቶ መቀበል መርህ መስራት እንደሚቻል በተግባር ማሳየቱ ያለንን ክብርና ሞጎስ በትግራይ ተወላጆች ማህበር በሰሜን አሜሪካና በሰሜን አሜሪካ ኗሪ በሆነው ሰላም፣ፍትህና ዴሞክራሲ ወዳድ ኢትዮጵያዊ ስም ማስተላለፍ እንወዳለን፡፡

- በሌላ በኩል ደግሞ ካለፈው 3ኛው ሃገራዊ ምርጫ ታላቅ ትምህርት በመቅሰም ጭፍን የጥላቻ ፖለቲካ ለአገራችን ህዝብ እርባና እንደማይኖረው በመረዳት የዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ጅማሮ ማጠናከር የሚቻለው በህገ-መንግስቱ ተገዝቶ በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ በመወዳደር የህዝብ ይሁንታን አክብሮ መቀበል አማራጭ የሌለው መሆኑን አምነውና ተቀብለው የጋራ ስምምነት ለመፈረም መ.ኢ.አ.ድ፣ ኢ.ዴ.ፓ፣ ቅንጅትና ኢ.ህ.አ.ዴ.ግን ወክለው በውይይቱ ተሳታፊ የነበሩትና ይህንን አመርቂ ውጤት ላስመዘገቡ አመራሮች ያለንን አድናቆትና አክብሮት ስንገልፅ ይህንን የተፈረመው ሰነድ እስከመጨረሻ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ገዢው ይሁን ተቀዋሚ ፓርቲዎች ያላቸውን ታላቅ ሃላፊነትና ህዝባዊ አደራቸውን ሙሉ በሙሉ እንደሚወጡ ተስፋ እያደረግን የዚህን በኢትየጵያ ታሪክ ታላቅ ስፍራ ያለው ምዕራፍ ኣካል ላልሆነው መድረክ የተባለው የተቃዋሚ ፓርቲ የወሰደው ኣቋም ከሰላማዊና ህጋዊ የትግል መድረክና መስመር እንዲሁም ልዩነቶችን በውይይት የማጥበብ ስልጡን ፖለቲካዊ ኣካሄድን ወደ ጎን የሚተውና በህገ-መንግስቱ ጥላ ከለላ ስር ማግኘት የሚችለውን ዕድል፣ መብትና ግዴታ ላይ ጥቁር ነጥብ እንደማስቀመጥ የሚቆጠር እንዳይሆን፣ የኢትዮጵያ ህዝብ በጉጉት የሚጠብቀው ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ሂደት እንዳያደናቅፍ ደጋግሞ እንዲያስብበትና አቋሙን ባፋጣኝ በማስተካከል ራሱን ወደ ሰላማዊ፣ ዴሞክራሲያዊና ነገሮችን በውይይት የመፍታት መድረክ እንዲገራ በትግራይ ተወላጆች ማህበር በሰሜን አሜሪካ ስም መልእክታችንና ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፡፡

የዴሞክራሲ፣ ፍትህና ልማት መረጋገጥ የረዥም ርቀት ጉዞና የሁሉም ህዝቦች ተሳትፎ ውጤት ናቸው!!

የትግራይ ተወላጆች ማሕበር ፅ/ቤት
ዋሽንግተን ዲሲ
ኖቨምበር 2/2009